# PANORAMA # 6

## የትዝብት አድማስ

## እርሱ ከሞተ  ነገር ተከተተ

በሀገራችን የቅርብ ዘመን የፖለቲካ ሂደት፥ የመንግሥት ሥልጣን በጨበጡት ሰዎች አካባቢ በተደጋጋሚ የሚሰማ ቧልት አለ። ይህም ለፖለቲካቸው መሰሪነት የሚጠቀምቡትና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ይረዳናል ብለው ከልብ ያመኑበት የዕድሜ ቀጥል ከንቱ ውዳሲያቸው ነው። ይህ ከንቱ ውዳሴ ፥ "እኛ ከሌለን ሀገሪቱ ትበታተናለች፥ ትፈርሳለች በመሆኑም የእኛ መቆየት ከሀገሪቱ ኅልውና ጋር መታየት አለበት" የሚሉት "ተጨፈኑና እናታልላችሁ" ዓይነት ግብዝነት ነው። የዚህ ዓይነት ፕሮፓጋንዳ መንስዔ፥ ያው ተደጋግሞ እንደሚነገረው፥ ገዥዎች በሕዝቡ ላይ ያላቸው ንቀትና ድንቁርና መሆኑ ደግሞ አንድና ሁለት አይባልም። ድንቁርና ሲባል፥ ገዥዎች ሕዝቡን በትክክል ካለማወቃቸው የመነጨ መሃይምነት ሳይሆን አይቀርም ብለው የሚደመድሙ የፖለቲካ ጠበብቶች አሉ። የመንግሥት ሥልጣን ይዤ ሀገር እመራለሁ የሚል ማነኛው የፖለቲካ ሰው፥ ከሁሉ በፊት መነሻ ማድረግ የሚገባው፥ እመረዋለሁ የሚለውን ሕዝብ ማንነት በትክክል ማወቅን ነበር።

ሕዝብን በትክክል ማወቅ ሲባል፥ የሀገሪቱን ታሪክና ሁኔታ፥ የዜጎቿን ጠባይና በኀርይ ፥ ባኅልና ዕምነት፥ ፍላጎትና ችግር፥ እንዲሁም ጠቅላላውን መስተጋብር ማለት ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን ይህ ሀቅ በተፈራራቂ የኢትዮጵያ ገዥዎች በኩል በጭራሽ የሚታወቅ አልነበርም። አሁንም አይደለም።

የአምባገነን መሪዎች መነሻም ሆነ ዓላማ፤ ማናቸውንም ኃይል በመጠቀም፥ ሕዝብን ረግጦ መግዛት ነው። ይህንን ዘዴ፥ በሥልጣን ለመቆየት ዋስትና ይሆንልናል ብለውም ያምኑበታል። ካጀማመራቸው፥ ሕዝብን በመጥላትና በመፍራት ላይ የተነሱ በመሆናቸው፥ በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ፥ የሚገዙትን ሕዝብ በመፍራትና በመጥላት ስለሚኖሩ፥ ዕድሜአቸውን ሁሉ የሚያሳልፉት የኅሊና ዕረፍት ሳያገኙ ነው ። ሕዝብን ከመፍራታቸው የተነሳ ጠልተውት ይኖራሉ። በፍርሃት ላይ የተገነባ ጥላቻ ደግሞ የሚወገደው፥ ፈሪውንና ጠይውን ሲያስወግዱት ብቻ ነው። ፍራቻን በጥላቻ፥ ድፍረትን በድንቁርና ሸፍኖ ሀገርን ለመግዛት መሞከር፥ ሕዝብን ከማጥፋት፥ ሀገርን ከማውደም የሚገታው ታምር ሊኖር አይችልም። ከጥንት ከጧቱ ይህንን ሀቅ ያልተረዳ የሀገር መሪ ነኝ ባይ ሥልጣን ላይ ከመውጣቱ በፊት ተጨንግፎ ቢቀር የሻለው ነበር። ሕዝብን ከጥፋት፥ ሀገርን ከውድመት እራሱንም ከመርገም ያድናልና! ምንም እንኳን የሀገር መሪዎች የመንግሥት ሥልጣን በመጨበጣቸው ብቻ በግንባር ቀደም ለክፉም ሆነ ለደጉ ተጠያቂዎች ናቸው

ሊባል ቢቻልም፥ ከሁሉ በላይ የሀገሩ ዕድል ወሳኝ ሕዝቡ መሆኑ ግን መታወቅ አለበት:: መሪዎች ኃላፊ ጠፊ፥ ሀጅ ና ነጓጅ፥ መጭና ተለዋጭ ሲሆኑ፥ ሀገርና ሕዝብ ግን ቋሚ አለትና መሠረት ናቸው:: ውሃ- ውሃው ሀጅ፥ አለቱ ቀሪ የሚባለውን ይትብሃል ማስታወስ ይጠቅማል::

በቅርቡ የተከሰተውን የሀገራችንን የፖለቲካ ሂደትና ዝንባሌ ስንታዘብ፥ ታዋቂው ደራሲ አቶ ከበደ ሚካኤል <u>አዝማሪና የውሃ ሙላት</u> በተሰኘው ግጥማቸው ያሰፈሩትን ቁም ነገር ያስታውሰናል:: ውሃ ዋና የማይችለው አዝማሪ ወንዙን ለመሻገር ፈልጎ የተጠቀመበት ስልት፥ ያው ሙያውን በመጠቀም ማሲንቆውን እየመታ የውሃውን ሙላት በግጥም ማባበል ነበር:: በባዶ ሜዳ ቆሞ ብቻውን ሲዘምር የተመለከቱ አንድ አዛውንት፥ ይህንን አዝማሪ “ምነው ወንድሜ ሰው በሌለበት በባዶ ሜዳ ብቻህን ለማን ነው የምታዘምረው? ” ብለው ቢጠይቁት፥ “አየ ጌታየ ወንዙ ስለሞላብኝ እኔም ውሃ ዋና ስለማልችል፥ ውሃው ከሁለት ተከፍሎ ቢያሻግረኝ ብየ በግጥም እያወደስኩት ነው” ብሎ ቢመልስላቸው፥ አዛውንቱም በበኩላቸው፥

“ ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ
ማን ያዳምጥሃል፥ ዉሃው ሙላት ሲያብድ
ይልቅስ ከእኔ ጋር ድልድዩን ተጠቅመን አብረን እንሂድ”

አሉት ይባላል::

እንደ አለቱ ታዛቢ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በየጊዜው እንደ ዕንግዳ ደራሽ፥ እንደ ውሃ ፈሳሽ እየከነፈ በመምጣትና በመሄድ ሀገር እያጠፉ ሕዝብ እየበደለ፥ እንደ ውሃ ሙላትም ሀብት እያግበሰበሰ የሚያልፈው የአምባገነኖች ሥርዓት መቼ መቆም እንዳለበት፥ እንዴትስ መወገድ እንደሚኖርበት ሕዝቡ የሚወስነው የራሱ ቆራጥ ውሳኔ እንደሚሆን መረሳት የለበትም:: ተወደደም ተጠላ ሕዝቡ መነሳቱ የታሪክ ሃቅ ነው:: መዕርግጥም ይህ ወቅት ርቆ አይርቅም::

ይህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ “ወያኔ ከሌለ ሀገሪቱ ትፈርሳለች” እየተባለ በተደጋጋሚ የሚወራው የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ቃጭል፥ ለጊዚያዊም ቢሆን ምናልባት ሊጠቅም የሚችለው ሁለት ክፍሎችን ብቻ ነው:: አንደኛው ያው እራሱን ወያኔን ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ ወደ ወያኔ ለመግባት የሚያቆበቁቡትን ተንበርካኪዎችን ነው:: በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሱት ክፍሎች፥ ወደ ወያኔ ለመሄድ፥ እንደማጠየቂያ የሚጠቀሙበት ወቅታዊ የእበላ ባዮች ፈሊጥ፥ ሀገራችን ልትፈርስ አንድ ሐሙስ ስለቀራት፥ ከወያኔ ጋር ሆነን ሀገር የማዳን ኃላፊነት አለብን ይላሉ:: ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው ግን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል ከሚሞክረው ከወያኔ ጋር አባሪ ተባባሪ ሆነው እነርሱም የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታ ለመናቅ መሞከራቸው ነው ::

የአንድ ሀገር መሠረቱ፥ የዚያ ሀገር ዜጋ መሆኑን አለመረዳት ወይም ተረድቶም ከሆነ፥ ይህንን አውቆ በሕዝብ በጎ ፈቃድና ትብብር፥ ይሁንታና ውሳኔ ያላገኘ “ ሀገር የማዳን” ርምጃ ለመውሰድ ማደናገር ትርፉ ትዝብ ይሆናል:: ምክንያቱም፥ ሀገርን ያስቆረሰ፥ ሕዝብን በጎሳና በቋንቋ የከፋፈለ፥ ኃይማኖትን ከኃይማኖት ያጋጨ፥ የሀገርን ሉዓላዊነት ያስደፈረ፥ ሕዝብን የጨፈጨፈና ያሰደደ፥ ያላስፈላጊ ጦርነት እያወጀ እልፍ አዕላፍ ዜጋ ያስመተረ ማን ሆኖ ነው፥ ከወያኔ ጋር ሆነን ሀገር እናድን ብሎ መነሳት?

ከላይ የተዘረዘሩት ሀቆች፥ በወያኔና ሌሎች ለሥልጣን በሚያቋምጡት ግለሰቦች መካከል ያልውን ክስተት ለመግለጽ ብለን እንጅ፥ ዛሬ ሀገሪቱ አደጋ ላይ አይደለችም ለማለት አይደለም:: በዕርግጥም ሀገራችን ከማንኛው ጊዜ በበለጠና በከፋ ሁኔታ ዛሬ የመጥፋቷ አደጋ እየፈጠጠ በመምጣት ላይ ነው:: በሻዓብያና በወያኔ መካከል የጦርነት መሰናዶ እያንዣበበ ይገኛል:: በሀገሪቱ የምሥራቁ ክፍል ያለው ሁኔታ እየገፋ ከሄደ ማንም ሊቆጣጠረው ከማይችልው ደረጃ የማይደርስበት ምክንያት አይኖርም:: የኢትዮጵያ የሩቅና ያካባቢ ባላንጣዎች የሀገሪቱን መበታተን ሂደት ከማጣደፍ ወደ ኋላ እንደማይሉ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: ይህንን ሁሉ ሁኔታ ተገንዝቦ ሀገርን ለማዳን ሕዝቡን የሚያስተባብር ማዕከላዊ መንግሥት አለ ለማለት አንችልም:: የደርግ መውደቅ የመጨረሻው አካባቢ ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም ሊባል አይቻልም:: ያ ደርግ የተሰኘ ፀረ ሕዝብ ቡድን፥ በመጨረሻው ሰዓት እንኳ ቢሆን ዕውቀት ገዝቶ በወቅቱ ሕዝቡን አስተባብሮ ሀገሪቱን ከአስገንጣዮቿ ማዳኑን ትቶ የመረጠው እስከ መጨረሽዋ ደቂቀ ድረስ ሕዝቡን እየጨፈጨፈ፥ ብሎም፥ ሀገሪቱን ለበላዒ ሰብ አጋልጦ መሸሽ ነበር:: ይህን ሁኔታ ሲያስታውሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዕግር እሳት ሆኖበታል:: ይህንን ሁኔታ እንዳይደገም ደግሞ የማነኛውም ሀገር ወዳድ ፍላጎት አይደለም ::

ያም ሆኖ ግን፥ ሀገርን እናድን በሚል ሰበብ ብቻ ግን የሀገሪቱን መጥፋት ከሚያባብሰው ጋር አባሪ ተባባሪ መሆን ግን የታሪክ መፀትና ሀገራዊ ወንጀል ይሆናል:: ታዲያ ይህንን እንቆቅልሽ ለመፍታት ምን መደረግ ይኖርበታል?

ብዙ ዙሪያ ጥምጥም ከመሄድ ተቆጥበን በአስቸኳይ ሀገርን ማዳን ካስፈለገ፥ መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያካተተ ሁኔታና መድረክ መፍጠር አንገብጋቢ ነው:: ይህ በየፊናው የሚራኮተው የተቃዋሚ ኃይል ያለውን የየግል ችግር ለጊዜወም ቢሆን ወደ ጎን ትቶ፥ ሳይውል ሳያድር ሀገርን ከጥፋት ለማዳን በሚለው አስቸኳይ ጥሪ ዙሪያ መሰባሰብ አለበት:: ከማንኛውም ጉዳይ የሚበልጠው የሀገር መኖር ስለሆነ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብና የተቃዋሚው ክፍል ተባብሮ በመነሳት ብሔራዊ ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት ከታሪክ ፀፀትና ወቀሳ ያድነዋል:: ሀገር ከጠፋች ሌላውም ሁሉ ከንቱ እንደሆነ የማይረዳ ዜጋ ይኖራል ብለን አናስብም፥ ከነወያኔ በስተቀር!

በማንኛውውም ወቅትና ሁኔታም ቢሆን ሀገርን ከማዳን የበለጠ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉም የሚረዳው ቢሆንም፥ ወያኔ ያጠፋትን ሀገር ከወያኔ ጋር ሆኖ

እንዴት ማዳን እንደሚቻል ዕንቆቅልሽ የሆነባቸው የሀገሪቱ ዜጎች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: በታሪክ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ሀገሩን ከቅኝ ገዥዎች ወረራ፥ ከውጭ ጥቃት፥ ከተፈጥሮ አደጋ ጥፋትና ከመሳሰሉት ሁሉ በመተባበር ያዳናት ለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን በሚያደርገው ሂደት ውስጥ፥ ከቻለ ከሀገር መሪዎች ጋር፥ ካልሆነ ግን በያካባቢው የራሱን የአርበኞች መሪዎች እየሰየመ ነበር እስካሁን ሀገሪቱን ከጥፋት አድኖ ያቆያት:: ምንም ምን ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከከሀዲያንና ከሀገር ሻጮች ጋር ተባብሮ አያውቅም:: ዛሬም ቢሆን ከአንዳንድ እበላ ባይ ግለሰቦችና ዓይናቸው በጥቅም ከታወረ ክፍሎች በስተቀር፥ ከወያኔ መሪዎች ጋር እየተባበረ አይደለም:: በአንፃሩ ግን፥ ዛሬ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞውን በልዩ ልዩ መንገድ እየገለፀ፥ እየታገለና መሥዋዕትም እየከፈለ ይገኛል:: እስኪ ለአንድ ቀን ጀምበር እንኳ ቢሆን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ ዕድል ያግኝና የወያኔ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን ይታይ!

የወያኔ አምባገነን ሥርዓት አንድ ሐሙስ ቀርቶታል የሚል ቅዠት ሊኖር ባይችልም፥ የሀገራችንን፥ የፖለቲካ ፥ የማኅበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ስናጤን፥ ብሎም በየቦታው ያለውን ሕዝባዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ስንገመግም፥ የሀገራዊው ትግል ርምጃ እየተፋጠነ እንደሚራመድ የታሪክ ሀቅ ነው:: በመነሻውና በመድረሻው ወያኔ ሲጫወትበት የነበረው የዘር የፖለቲካ ቁማር መጫወቻ ካርዱም በየጊዜው እየወየበበት በመሄድ ላይ ነው:: የበላይ ጠባቂዎችም ቢሆኑ፥ "አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት" በሚለው ስልታቸው፥ ነገር ዓለሙ ሁሉ በመላሸቱን ሲያዩ እንደ ነጋበት ጅብ ጥለውት እንደሚሄዱ ካለፈው ታሪካቸው መረዳት ይቻላል:: የዓለም አቀፍን ግንኙነት ባኅርይንና የዲፕሎማሲውን ዓብነት በሚገባ መረዳት ከተቻለ፥ ሊኖር የሚችለው ቋሚ ጥቅም እንጅ፥ ቋሚ ወዳጅም ይሁን ወይም ቋሚ ጠላት የሚባል ፈሊጥ አለመኖሩን ነው:: በመሆኑም፥ ምዕራባውያን፥ አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት፥ የዛሬ አገልጋያቸውን፥ ሲያገለገላቸው የነበረበትን የወር ደመዎዝ እንኳ ሳይከፍሉት በሚያስገርም ፍጥነት አጋልጠው፥ በሌላ አዲስ አገልጋይ እንደሚተኩት የተረጋገጠ ነው:: ለዚህም ነው መሰል፥

ያገራችን ሰው " ፉርኖውም ያልቅና፥ አኒችው ያልቅና፥
ጣሊያን ይሄድና፥
ያስተዛዝበናል ይኸ ቀን ያልፍና::"
ነግሬሽ ነበረ በአጥር ተንጠልጥየ
ፈረንጅ ቁባት እንጅ ባል አይሆንም ብየ:: " ያለው::

በታሪክ አጋጣሚዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአያሌ ባንዳዎችና ሀገር ሻጮች ክህደት እየታዘበ የኖረ በመሆኑ ፥ በወያኔ ዙሪያ የተኮለኮሉትንና ወደፊትም ለመኮልኮል የወር ተራቸውን የሚጠብቁትንም እንዲሁ እየታዘባቸው ይገኛል:: በመሆኑም፥ " በአሁኑ ወቅት፥ ወያኔ ከሥልጣን ከወረደ፥ ሀገሪቱ ልትበታተን ትችላለችና ከወያኔዎቹ ጋር አባሪ ተባባሪ መሆን አለብን" በሚል አሳፋሪና ተልካሻ ማጠየቂያ የዘረኞችን ሥርዓት ዕድሜ ለመቀጠል የሚደረገውን

ጥድፊያ ሁሉም በያለበት ሊያወግዘው ይገባል፡፡ ሀገር የሚድነው በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቃትና ትጋት፥ ኅብረትና ኃይል እንጅ፥ ከመጀመሪያውኑ አንስቶ ኢትዮጵያን ሲያጠፋ ከነበር ከይሲ ዘረኛ የወያኔ ቡድን ጋር በመተባበር አይደለም ፡፡ የሰው ልጅ ሰብዕናውም ሆነ ህይወቱ እንደ አላቂና ጠፊ ቆሳቆስ የትም መውደቅ የለበትም የሚባል አባባል መኖሩን ብንረዳም፡ በአንፃሩ ግን "ያለ እርሱ ምንም ነገር ሊሳካ አይችልም" ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም፥ ወያኔ ከለለ ነገር ተከተተ የሚበል ቧልታና ቀልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመጤፍ የሚቆጥረው ጉዳይ አይደለም፡፡

" ጀግኖች በመሩለም ሀገር ያድናሉ፥
የኢትዮጵያ ጠላቶች በዕርግጥ ይወድማሉ" !!!!!!!!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ ሀገሩን ከጥፋት እንዲያድን ሀገራዊ ጥሪያችንን አናስተላልፋለን፡፡

ታህሳሥ 19 2000 ዓም